## ኖቬምበር 2017 QuickNotes ዜና መልእክት ቁ. 1

**በአገልግሎት/በሥራ ልቆ/ቃ የሚታይ/የምትታይ መምህር፣ ርእሰ መምህር፣ ወይም ድጋፍ ሰጪ የሥራ ባልደረባ ያውቃሉ?**

*ማጠቃለያ፡- ወላጆች እና የማህበረሰብ አባላት፤ የላቀ/ምርጥ እና ብሩህ አእምሮ ያለውን/ያላትን ሠራተኛ ለማጨት/ለመጠቆም ጊዜው አሁን ነው።* MCPS *ወደር የሌለው አገልግሎት በማበርከት ላይ ለሚገኙ ሠራተኞች ያለውን አክብሮት ለመግለጽ ልዩ ልዩ ሽልማቶችን አዘጋጅቷል። ማመልከቻዎችን በሚቀጥለው ወር እና እስከ ጃኑዋሪ* 2018 *ድረስ ማቅረብ ይቻላል። ማመንታት የለብዎትም፤ ይጠቁሙ!*

ሽልማቶች የሚሰጡበት ወቅት ደርሷል! የላቀ/ምርጥ መምህራን እና ርእሰ መምህራን ለበርካታ ሽልማቶች ለመወዳደር እንዲታጩ ጥቆማ ለማቅረብ አሁን ክፍት ነው። እነዚህም የሚከተሉት ናቸው—

**ማሪያን ግሪንብላት በማስተማር ክህሎት የላቀ የመምህር ሽልማት** ("The Marian Greenblatt Excellence in Education Master Teacher Award") ከሙዋዕለህፃናት እስከ 12ኛ ክፍል ድረስ ከሚያስተምሩ የሙሉ-ጊዜ መምህራን ውስጥ የተማሪዎችን የክንዋኔ ክፍተት በማጥበብ ለስኬት እንዲበቁ በማስቻል ወደር የሌለው ውጤት ያስመዘገቡ ሦስት መምህራን ሽልማት ይሰጣል። ከመምህራን የላቀ ሽልማት አሸናፊዎች ውስጥ አንዱ/ዷ የ MCPS የዓመቱ መምህር/ት በመሆን ይመረጣል/ትመረጣለች። ለእያንዳንዱ ደረጃ፡- ለአንደኛ ደረጃ/ኤሌሜንታሪ፣ ለመካከለኛ እና ለሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት - አንድ የሽልማት አሸናፊ ይኖራል። ተጨማሪ መረጃ [እዚህ] ይገኛል። **የጊዜ ገደብ፡- 4 p.m. ዓርብ፣ ጃኑዋሪ. 12፣ 2018**

The Marian Greenblatt Excellence in Education Rising Star Teacher Award **በምጥቀት ላይ የሚ(ምት)ገኝ ኮከብ መምህር ሽልማት** ከሙአለህፃናት እስከ 12ኛ ክፍል የተማሪ ስኬት በማራመድ ከፍተኛ ውጤት ላስመዘገበ/ች የአንደኛ-፣ ሁለተኛ-፣ ሶስተኛ- ወይም ለአራተኛ ዓመት ቋሚ መምህር እውቅና ይሰጣል። ተጨማሪ መረጃ [እዚህ] ይገኛል። **የጊዜ ገደብ፡- 4 p.m. አርብ፣ ጃኑ. 12፣ 2018**

***[የዋሽንግተን ፖስት/The Washington Post የዓመቱ መምህር ሽልማት]*:**
*የዋሽንግተን ፖስት/The Washington Post* የዓመቱ መምህር ሽልማት ከሙዋእለህፃናት እስከ 12ኛ ክፍል ድረስ ሙሉ ጊዜ ለሚያስተምር/ለምታስተምር መምህር/ት እውቅና ይሰጣል። መምህሩ/ሯ የእያንዳንዱን ተማሪ ግላዊ የትምህርት ፍላጎት መረዳት አለበ(ባ)ት፣ ያላቸውን ልዩ ተሰጥኦ/ችሎታ ማደፋፈር እና ጥረታቸውን ማሳደግ መቻል። እርሱ ወይም እርሷ በትምህርቱ ጥልቅ እውቀት እንዲያሳይ/እንድታሳይ እና ከተማሪዎች ጋር በውጤታማነት የመጋራት ችሎታ ይኖረዋ(ራታ)ል። "Sean Pang" ከሮክቪል ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ያለፈው ዓመት አሸናፊ ነበር። Sean Pang of Rockville High School was last year's winner. **የጊዜ ገደብ፡- 4 p.m. ዓርብ፣ ጃኑዋሪ. 5፣ 2018**

***[የዋሽንግተን ፖስት/Washington Post የዓመቱ ርእሰ መምህር ሽልማት]*:**
**ይህ ሽልማት እለት ተእለት ካለባቸው የስራ ኃላፊነት መወጣት አልፈው "ልዩ የትምህርት አካባቢ" ለሚፈጥሩ ርእሰ መምህራን እውቅና ይሰጣል። እጩዎችን መምህራን፣ ተማሪዎች፣ የቀድሞ ተማሪዎች፣**

ወላጆች፣ አስተዳዳሪዎች፣ ወይም ሰፊው ህብረተሰብ ማቅረብ ይችላሉ። **የጊዜ ገደብ፡- 4 p.m. አርብ፣ ጃኑ. 5፣ 2018**

[የሻይርልይ ጄ. ሎውሪ ስለ ማስተማርህ/ሽ አመሰግናለሁ ሽልማት/The Shirley J. Lowrie Thank You for Teaching Award]"
የሻይርልይ ጄ. ሎውሪ ስለማስተማርህ/ሽ አመሰግናለሁ" ሽልማት/The Shirley J. Lowrie Thank You for Teaching Award ወደር የሌላቸው የአንደኛ ደረጃ ት/ቤት (ኤለመንታሪ ት/ቤት) መምህራን፣ ከቅድመ-ሙዋእለ ህፃናት እስከ 5ኛ ክፍል በመማሪያ ክፍል ውስጥ በየቀኑ በቀጥታ ከተማሪዎች ጋር አብረው የሚሰሩ፣ በትምህርቱ ላይ በቂ እውቀት ያላቸው፣ እና ትምህርቱን ለተማሪዎች የማስተላለፍ ብቃት ያሳዩ/ያላቸው። **የጊዜ ገደብ፡- 4 p.m. አርብ፣ ጃኑ. 5፣ 2018**

[የሱፐር ኢንተንዳንቱ ዓመታዊ ወደርየለሽ ሰው የላቀ እና ህብር ሽልማት/The Superintendent's Annual Mark Mann Excellence and Harmony Award]፣
ይህ ሽልማት የ MCPS ርእሰ መምህራን እጅግ በጣም ጥሩ ትምህርት፣ መልካም ሰብአዊ ግንኙነት፣ እና ማህበረሰቡን በመድረስ እመርታ ላሳዩት ልዩ ሽልማት ይሰጣል። **የጊዜ ገደብ፡- 4 p.m. ዓርብ፣ ጃኑዋሪ 5፣ 2018**

የ [2018 የዓመቱ ድጋፍ ሰጪ ሠራተኛ/2018 Supporting Services Employee of the Year ፡-]
ይህ ሽልማት ለ MCPS የላቀ አስተዋጽኦ ላበረከተ/ች የድጋፍ ሰጪ አገልግሎት ሠራተኛ የሚሰጥ ነው። ተሰያሚዎች ቋሚ ሰራተኞች መሆን አለባቸው በ MCPS የሶስት አመት አገልግሎት እንዲኖራቸው ያስፈልጋል። ስለ ተሰያሚዎቹ በበርካታ የመመዘኛ መስፈርት ማጣሪያ ይደረጋል። የሚያካትተውም:- ተነሳሽነት/ትጋት፣ የፈጠራ ችሎታ፣ ጥበብ እና የዓላማ ፅናት፣ ለተማሪዎች፣ ለሠራተኞች እና/ወይም ለአጠቃላይ ማህበረሰቡ ያደረገው/ያደረገችው አስተዋጽኦ፣ ከበሬታ/አክብሮት እና አድናቆት፣ የአመራር ብቃት፣ እና ከሰዎች ጋር አብሮ የመስራት ጥበብ። **የጊዜ ገደብ:- 5 p.m. ሐሙስ, ዲሴምበር 21** የመጠቆሚያ ቅጽ [እዚህ] ይገኛል።

**ሱፐርኢንተንዳንቱ እና የቦርድ ፖሊሲ አስተዳደር/ማኔጅመንት ኮሚቴ ለ 2018–2019 አዲስ ቀን መቁጠሪያ/ካላንዳር አማራጭ ሃሳብ/አስተያየት አቅርበዋል።**

የትምህርት ቦርድ አዲስ በቀረበው የቀን መቁጠርያ/ካላንዳር አስተያየት/ሃሳብ ላይ ኖቬምበር 14 በሚያካሄደው ስብሰባ ለመነጋገር አጀንዳ ተይዟል። የቀረቡት ሃሳቦች በ MCPS ድረ-ገጾች ላይ ይገኛሉ።

*ከዚህ በታች ያለው ከዋና የሥራ ኃላፊ አንድሪው ዙከርማን (Andrew Zuckerman) ስለ 2018–2019 የቀን መቁጠርያ/ካላንዳር አሰራር/ዝግጅት የቀረበ ሃሳብ ነው።*

ባለፈው ዓርብ እለት እንደገለጽኩላችሁ፣ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ማኔጅመንት ኮሚቴ ለማክሰኞ ኦክቶበር 24፣ ስለ 2018-2019 የት/ቤት ቀን መቁጠሪያ/ካላንዳር ለመነጋገር የስብሰባ ቀጠሮ ተይዞ ነበር። ትላንትና በተካሄደው በዚህ ስብሰባ ላይ፣ ሠራተኞች ከሱፐርኢንተንደንቱ በቀረበው የ2018-2019 የትምህርት ዓመት ቀንመቁጠሪያ/ካላንዳር ላይ ሃሳብ/አስተያየት አቅርበዋል። በተጨማሪ፣ የቦርድ ፖሊሲ ማኔጅመንት ኮሚቴ አባላት ኖቬምበር 14 ለሚደረገው የአጠቃላይ ቦርዱ የሥራ ስብሰባ ሠራተኞች 3

ተጨማሪ የቀን መቁጠሪያ አማራጮችን እንዲያዘጋጁ ጠይቀዋል። በኦክቶበር 24፣ 2017 የቦርድ ፖሊሲ ማኔጅመንት ስብሰባ ላይ የቀረበውንና የተካሄደውን ውይይት መመልከት ይችላሉ። አዲስ አስተያየት የቀረበውንም ቀን መቁጠሪያ/ካላንዳር ከዚህ መመልከት ይችላሉ ።

በዶ/ር ስሚዝ (Dr. Smith) እና በቦርዱ ፖሊሲ ማኔጅመንት ኮሚቴ የቀረበው የቀን መቁጠሪያ/ካላንዳር አስተያየት/ሃሳብ፣ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት የተሰበሰቡ በርካታ አስተያየቶችን ተመርኩዞ ነው። እያንዳንዱ የሚፈልገዉ በሚቀጥለው ዓመት ያሉትን በቁጥር የተወሰኑ ቀኖችን በተቻለ መጠን በማብቃቃት በርካታ ፍላጎቶችን ለማሟላት ነዉ። እስካሁን ምናልባትም እንደምታወቁት በሴፕቴምበር 3፣ 2018 (የሠራተኞች ቀን/ Labor Day) እና ጁን 14፣ 2019 (በሜሪላንድ ስቴት 2018-2019 ለት/ቤት ሊፈቀድ የሚችል የመጨረሻው የትምህርት ቀን/the last allowable day of school in the state of Maryland for 2018-2019) መካከል ያሉ ስድስት ቀናት ሲሆኑ ፣ እነዚያ ቀናት ለትምህርት መስጫ ሳይሆን ሌሎች አስፈላጊ ስራዎች ለምሳሌ የስፕሪንግ እረፍት፣ ወይም ለተማሪዎች ውጤት/ማርክ የሚዘጋጅበት እና እቅድ/ፕላን የሚሰራባቸው ቀኖች ሊሆኑ ይችላሉ። ያሉትን እነዚህን ውስን ቀኖች ለተለያየ/በርካታ ፍላጎቶች እንዴት መጠቀም እንደሚቻል ለመወሰን በጣም ይከብዳል፣ እናም ከእያንዳንዱ የተሰጠውን ምላሽ አስተያየት እናደንቃለን።

የ 2018-2019 የትምህርት ዓመት ቀን መቁጠሪያ/ካላንዳር ለማዳበር የሚቀጥለው ደረጃ ኖቬምበር 14፣ የቦርድ ጠቅላላ ጉባኤ በቀረቡት አዲስ የቀን መቁጠሪያ/ካላንዳር ሃሳብ/አስተያየቶች ላይ የሚያደርገው ውይይት ይሆናል። በእኔ ግምት፣ ኖቬምበር 14 በሚካሄደው የቦርድ ስብሰባ ላይ የ2018-2019 የትምህርት ዓመት ቀን መቁጠሪያ/ካላንዳር የማጽደቂያ ድምፅ ይሰጥበታል።

አንድርው ዙከርማን Andrew Zuckerman
ዋና የሥራ መኮንን Chief Operating Officer
የሞንጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች
(Montgomery County Public Schools)

ወቅታዊ መረጃ/ኢንፎርሜሽን ስለ .. ያግኙ። የት/ቤት ቀን መቁጠሪያ ድረ-ገጽ

ለኖርዝኢስት ኮንሶርሺያ (Northeast Consortium (NEC))፣ለታችኛው ካውንቲ ኮንሶርሽያ (Downcounty Consortium (DCC))፣እና ለመካከለኛ ደረጃ ማግኔት ፕሮግራም (Middle School Magnet Consortium (MSMC)) የትምህርት ምርጫ የሚደረግበት የጊዜ ገደብ ዓርብ ኖቬምበር 3 Friday, Nov.3 ሲሆን ለሮቤርቶ ክለመንቴ መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት እና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ማመልከቻ የሚቀርብበት የጊዜ ገደብም ኖቬምበር Friday, Nov.3 ነው።
http://www.montgomeryschoolsmd.org/schools/msmagnet/

የበለጠ መረጃ ለማግኘት ቀጥሎ ያሉትን ድረ-ገጾች ይመልከቱ።

NEC: http://www.montgomeryschoolsmd.org/schools/nec/
DCC: http://www.montgomeryschoolsmd.org/schools/downcounty/
MSMC: http://www.montgomeryschoolsmd.org/schools/msmagnet/

http://www.montgomeryschoolsmd.org/departments/enrichedinnovative/events/high.aspx

**myMCPS Portal የስርዓተ-ትምህርት ሠነዶች/ካሪኩለም ዶኩሜንቶች እና ሌሎች መረጃዎች ተጨምረውበታል።**

ተጨማሪ የተደረጉት መረጃዎች፣ እንግሊዝኛ ቋንቋ ስነጥበብ፣ ሂሳብ እና ሣይንስ፣ ሠነዶች ሲሆኑ ወላጆች እና ተማሪዎች በግልፅ እንዲረዱት ይጠቅማል።

ከወላጆች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት myMCPS Parent እና Student Portal የተማሪዎችን የትምህርት ሂደት የበለጠ ለመደገፍ፤ አሁን የካሪኩለም ሠነዶች እና ሌሎች መርጃዎች ተካተዋል/ተጨምረውበታል። የ MCPS ወደ portal መሸጋገር ለወላጆች/አሳዳጊዎች እና ለተማሪዎች ስለ ካሪኩለሙ በበለጠ በግልጽነት የማወቅ እድል ይሰጣቸዋል። parent portal ከዚህ በፊት ት/ቤቶች ስለ ማርክ/ውጤት፣ ስለ ተማሪዎች የትምህርት ክትትል ሁኔታ፣ ስለ ጊዜ ሠሌዳ አወጣጥ እና ሌሎችም ነገሮች የመጀመሪያ ከቤት-ወደ-ት/ቤት የመገናኛ አውታር መጠቀሚያ በነበረው በ "Edline" ቦታ ተተክቷል።

ከኦክቶበር አጋማሽ ጀምሮ MCPS በ portal መገናኛ አውታር ላይ የካሪኩለም ሰነዶች እና ማሻሻያዎችን፣ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ስነ-ጥበብ፣ ሂሳብ፣ እና ሳይንስ ትምህርቶች በመጀመር እንዲለጠፉ አድርጓል /posted።

- ለአንደኛ ደረጃ/ኤለመንታሪ፣ የምንባብ እና የሂሳብ ሠነዶች፣ ከሙዋእለ ህፃናት እስከ 5ኛ ክፍል፣ እና ሳይንስ ከ4ኛ - 5ኛ ክፍሎች ይገኙበታል/posted ። የአንደኛ ደረጃ ትምህርት መርጃዎች እዚህ ይገኛሉ። https://sites.google.com/a/mcpsmd.net/mcps-elementary-curriculum-parent-resources/home

- ለሁለተኛ ደረጃ የትምህርት መርጃዎች/secondary level፣ እንግሊዝኛ ከ 6-12 ክፍሎች፣ እና የሂሳብ ኮርሶች ከ6 እስከ አልጄብራ II ተለቀዋል/released። የሁለተኛ ደረጃ የትምህርት መርጃዎች እዚህ ይገኛሉ። https://sites.google.com/mcpsmd.net/secondaryparentresources/home

ዓመቱን በሙሉ ተጨማሪ ካሪኩለም/የትምህርት መርጃዎች ይለጠፋሉ/will be posted።

**ሱፐርኢንተንዳንቱ ለት/ቤቶች ግንባታ የ$1.818 ቢሊዮን እቅድ አቅርበዋል።**

የስድስት ዓመቱ እቅድ የተማሪ ቅበላ እድገት ለማስተናገድ እና ያረጁ ተቋማትን ለመጠገን/ለማሳደስ ይውላል። በቀረበው አስተያየት እቅድ ላይ 30 የአቅም ግንባታ ፕሮጀክቶች፣ እና አሁን ባለው የግንባታ ማሻሻያ/የካፒታል በጀት ላይ የ$74 ሚሊዮን ዶላር ጭማሪ አለው።

ሱፐር ኢንተንደንት ጃክ አር. ስሚዝ/Superintendent Jack R. Smith፣ ለMCPS  የስድስት ዓመት የት/ቤት ግንባታ፣  30 የአቅም ግንባታ ፕሮጀክቶች ማሰሪያን የሚያካትት በአጠቃላይ የትምህርት ስርዓት ውስጥ ያሉትን የቦታ ችግሮች ለማቃለል/ የ$1.818 ቢሊዮን ዶላር የበጀት እቅድ አቅርበዋል። ሱፐርኢንተንደንቱ ለ2019–2024 የበጀት ዓመት ያቀረቡት $74 ሚሊዮን ተጨማሪ የካፒታል ማሻሻያ በጀት CIP ፣ በሚቀጥሉት ስድስት ዓመታት በዲስትሪክቱ ውስጥ በፍጥነት እያደገ የመጣውን የተማሪ ምዝገባ/ቅበላ ለማስተናገድ ያስችላል።

"ለት/ቤቶቻችን የሚያስፈልጋቸውን መገልገያዎች በፍጥነት ምላሽ መስጠት እንዳለብን እና የበጀት አጠቃቀማችንም የካውንቲውን የወጪዎች ህግ መሠረት በማድረግ ተጠንቅቀን የመስራት ፍልሚያ እንዳለብን, "ስሚዝ/Smith ገለጹ።" ይህ በእቅድ ደረጃ የቀረበ ሃሳብ/recommendation በሞንጎመሪ ካውንቲ የህዝብ ት/ቤቶች ፍላጎቶች ውስጥ ወሳኝነት ያላቸው የአቅም ግንባታን የማሻሻል ፕሮጀክቶች ያሟላል።"

ለ 2017-2018 የትምህርት ዓመት የተማሪዎች ቁጥር 161,936 ይሆናል። በአንድ ዓመት የተማሪዎች ቁጥር በ2,926 ይጨምራል/ያድጋል። ባለፉት 10 ዓመታት፣ የተማሪዎች ቁጥር በ 24,191 አድጓል/ጨምሯል።

*ሱፐርኢንተንዳንቱ ያቀረቡትን የ 2019–2024 የበጀት አመት  የካፒታል ማሻሻያ ፕሮግራም/ እቅድ ያንብቡ*

**የአንደኛ ደረጃ/ኤለመንታሪ ት/ቤት ፕሮጀክቶች**

የስድስት ዓመት የካፒታል ማሻሻያ ፕሮጀክት/CIP የሚያካትተው ሦስት አዲስ የአንደኛ ደረጃ/ኤለመንታሪ ት/ቤቶች እና አራት አዲስ  የኤለመንተሪ ተጨማሪ ፕሮጀክቶችን (Cresthaven, DuFief, Ronald McNair and Roscoe R. Nix elementary schools) ያጠቃልላል። ከታቀዱት አዲስ ት/ቤቶች ውስጥ ሁለቱ በክላክስበርግ ክላስተር፣ እና አንድ በ ሪቻርድ ሞንጎመሪ ክላስተር ይሆናሉ። እነኚህ ፕሮጀክቶች ቀደም ሲል ከፀደቁት 11 ፕሮጀክቶች ሌላ በተጨማሪ የታቀዱ ናቸው።

**የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ፕሮጀክቶች**

በመካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች የካፒታል ማሻሻያ ፕሮጀክት/CIP  የሚያካትተው አራት ቀደም ሲል የፀደቁትን እና ሁለት አዲስ የታከሉትን የመጨመሪያ/ቅጥያ ፕሮጀክቶችን ነው። ሁለት አዲስ የተጨመሩት ለParkland Middle School and Silver Spring International Middle School፣ ሁለቱም ከመጠን በላይ/በተጨናነቀ ሁኔታ አገልግሎት እየሰጡ ናቸው።

**የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ፕሮጀክቶች**

ለሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የቀረበው እቅድ የሚያካትተው ሁለት ቀደም ሲል የፀደቁ እና ሁለት አዲስ የታከሉትን ተጨማሪ ፕሮጀክቶችን ነው። አዲስ የተጨመሩት የ Northwood High School

በማስፋፋት 2,700 ተማሪዎችን እንዲይዝ የ (1,200 መቀመጫዎች ጭማሪ) እና የ John F. Kennedy High School ለማስፋፋት ነው።

በተያዘው እቅድ-ሃሳብ መሠረት፣ በሁለቱም የ Downcounty Consortium እና the Walter Johnson Cluster ያለውን መጨናነቅ ለማቅለል የቀድሞውን Charles W. Woodward High School እንደገና ለመክፈት ነው። በተያዘው እቅድ መሠረት ጌትስበርግ ከተማ በሚገኘው Crown site ተጨማሪ አዲስ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት መገንባትን ያካትታል።
ካውንቲ አቀፍ ፕሮጀክቶች

*የተያዘው የበጀት ዓመት 2019 ካፒታል በጀት እና ለበጀት ዓመት 2019-2024 የካፒታል/ህንፃዎች ሥራና ማሻሻያዎች ፕሮግራም* በመዋቅር-አቀፍ /systemwide needs ያሉትን ፍላጎቶች፣ ስርዓታዊ ፕሮጀክቶቻችንን በመጨመር ጣራዎችን መቀየር/መተካት እና Planned Life-cycle/ ዕቅዳዊ የንብረት ህይወት ኡደት መተካት/መቀየር የመሳሰሉትን ያካትታል። በተለይም በእቅድ የተያዘው ባጀት አገልግሎት የጨረሱ ማሞቂያዎችን፣ አየር-ማናፈሻዎችን፣ እና አየር ማቀዝቀዣዎችን (Heating, Ventilation, and Air Conditioning (HVAC)) ለመለወጥ/ለማሻሻል በርካታ/ትርጉም ያለው የገንዘብ ጭማሪ መጠን ተይዟል።

*ለትምህርት ቦርድ የቀረበውን ሃሳብ ይመልከቱ*
http://www.montgomeryschoolsmd.org/press/index.aspx?pagetype=showrelease&id=8113&type=&startYear=&pageNumber=&mode=

በዶ/ር ስሚዝ የቅርብ ጊዜ ብሎግ ላይ/Dr. Smith's latest blog ስለ አክብሮት/መከባበር ዋጋ መስጠት ያለበት ዋና መሠረታዊ እሴት መሆኑን ይገልጻሉ። መከባበር/አክብሮት፤ በጣም ጥሩ የትምህርት አካባቢን ይፈጥራል፣ ሚዛናዊነት በማረጋገጥ ከባልደረቦች ጋር፣ ከተማሪዎች ጋር፣ እና ከማህበረሰቡ አባላት ጋር ሙያዊ የሆነ ግንኙነት ለመፍጠር ይረዳል።

በቅርቡ ከ Merle Cuttitta, president of SEIU Local 500 ጋር ተነጋግረን ነበር። ይህ ድርጅት የ MCPS በትምህርት ሙያ አጋዥ ሠራተኞችን (paraeducators)፣ ትራንስፖርቴሽን፣ የምግብ አገልግሎት፣ የህንፃ አገልግሎት፣ የጥገና ሥራዎች፣ መገናኛ እና ቴክኖሎጂ፣ እና ጽ/ቤትን እና የአስተዳደር ሠራተኞችን ይወክላል። በየወሩ እየተገናኘን የተማሪዎችን የመማር ሂደት እና ሠራተኞቻችንን ለመደገፍ እንዴት በጋራ ለመስራት እንደሚቻል ለመነጋገር/ለመረዳት እንሞክራለን። በዚህ በተወሰነ ቀን፣ በት/ቤቶቻችን ስርዓት እና በማህበረሰባችን እየተደረጉ ያሉ ጥሩና መልካም ነገሮችን አንስተን ተነጋግረናል፣ እንዲሁም ደግሞ ገና በጋራ መስራት ያሉብንን ነገሮች አቅርበናል።

አንዱ የተወያየንበት ጉዳይ ስለ "አክብሮት/መከባበር" ነው።

አክብሮት ደስ የሚያሰኝ ፅንሰ ሃሳብ/እሳቤ ነው። ከብዙ ዓመታት በፊት የሆነ አባባል መስማት የተለመደ ነበር፣ *"ከበሬታ ለማግኘት አክብሮት መስጠት አለብህ/ሽ"።* ይሁን እንጂ እኔ ሁልጊዜ የሚገርመኝ ነገር፣ ይህ እንደ ምክንያት/ሰበብ ወይም እንደ ሃላፊነት ከተሰጠ። የትኛው ይቀድማል? እና እኔ ለአንድ ሰው

አክብሮት ብሰጠውና ያ ሰው እኔን መልሶ እንዳላከበረኝ ከተሰማኝ/ከገመትኩ፣ መልሼ ያንን ሰው ለማቅለል/ላለማክበር ፈቃድ/ምክንያት ይሆናል?

ከተማሪዎች ጋር፣ ከቤተሰብ እና የስራ ባልደረቦች ጋር በሚኖረን ሙያዊ ግንኙነት፣ ሁልጊዜም አክብሮት በተሞላበት መንገድ ማከወን በጣም አስፈላጊ ነው። ምንም ልዩነት የለም፣ ምንም ምክንያት/ሰበብ የለም። እያንዳንዱ/ሁሉም አስፈላጊ ነው።

በእርግጥ እኔ እንደማምነው፣ አክብሮት ዋጋ ከሚሰጣቸው አምስት መሰረታዊ ዋና እሴቶቻችን አንደኛው እና ዋነኛው/ቀዳሚው ነው ። (መማር፣ ግንኙነት፣ አክብሮት፣ የላቀ ችሎታ፣ እና ሚዛናዊነት)። እንደሚመስለኝ ማናቸውም ሌሎቹ ዋና እሴቶቻችን ያለአክብሮት የሚሆኑ አይመስለኝም። በጣም ጥሩ የትምህርት አካባቢ ለመገንባት መሠረት ይሰጠናል፣ ሚዛናዊነትን ያረጋግጣል፣ ከምናገለግላቸው እና ከሥራ ባልደረቦቻችን ጋር ሙያዊ  እና ቀጣይነት ያለው ግንኙነት ይፈጥርልናል ።

እያንዳንዳቸዉ እነዚህ ዋና እሴቶቻችን በመማሪያ ክፍሎች፣ በት/ቤቶች፣ በካፍቴሪያዎች፣ በየቢሮዎቻችን፣ እና በአትሌቲክስ/ስፖርት ሜዳዎች፣ እንዲሁም በት/ቤት አውቶቡሶች-በሌላ አባባል፣ በማናቸውም ጊዜና የትም ቦታ ከሌሎች ጋር በምንሠራበት ህይወት አክብሮት መስጠት ለሁሉም ትምህርት ሊሆን ይችላል። ሚዛናዊነት ያድጋል/ይዳብራል።

በ MCPS፣ ስለ መከባበር/አክብሮት እና ስለሚዛናዊነት ብዙ እናወራለን፣ ነገር ግን ፅንሰሃሳቡን ትርጉም ያለው ለማድረግ፣ እያንዳንዳችን እለት ተእለት ከተማሪዎቻችን ጋር፣ ከቤተሰብ እና ከባልደረቦቻችን ጋር በስነ-ምግባራችን እና በተግባር ልንኖረው ይገባል። "ተማሪዎችን ማግኘት የሚገባቸውን እድል ስንነፍጋቸው አክብሮት ነው? ወይስ ሚዛናዊነት ነው?" ደግመን ደጋግመን ራሳችንን መጠየቅ ይኖርብናል። በትምህርታቸው መረዳት የሚገባቸውን ተማሪዎች ችላ ስንላቸው ወይም የሥራ ጓዶቻችንን ፊት መንሣት/ማስወገድ ወይም ያለርህራሄ/ደስ የማይል ባህርይ ስናሳያቸው አክብሮት እያሳየናቸው ነው?"

*"ክብር ለማግኘት ክብር መስጠት"* የሚለው ሃሳብ፣ በቂ ምክንያት/ሰበብ ነው ወይስ ሃላፊነት? ለእኔ፣ አክብሮት መስጠት በየቀኑ መደረግ ያለበት ሃላፊነት፣ በተለይም አክብሮት አይገባውም/አይሰጥም ብዬ የማስበው ሰው ሲያጋጥመኝ ማክበር ተገቢ እንደሆነ ሃላፊነት ይሰማኛል። በዚህ ዋና እሴት ላይ የተመሰረተ ባህል በቀጣይነት ለማዳበር/ለመገንባት፣ አብረን እያንዳንዳችን መደጋገፍና መቀጠል አለብን። ይህንን ካደረግን፣ በእውነትም ለተማሪዎቻችን እጅግ በጣም ጥሩ ትምህርት ልንሰጣቸው እንችላለን።

P.S. [ይህ ቪዲዮ ](http://bit.ly/MCMD2017)ልምድን በመለዋወጥ እንዴት መከባበርና ግንኙነትን ለማዳበር እንደሚቻል ግልጽና ለዛ ያለው ሃሳብ ይሰጣል። http://bit.ly/MCMD2017

**የኮሌጅ የበአል/ትርኢት (ኮሌጅ ፌር) ወራት ተጧጧፏል!**

የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ላሏቸው ወላጆች ስለ ኮሌጅ፣ ስለ ስኮላርሽፕ እና ስለ ፋይናንስ እርዳታ በይበልጥ ለመማር/ለማወቅ ብዙ እድል እየመጣ ነው።

በዚህ ፎል፣ ወላጆችና ተማሪዎች ስለ ድህረ-ሁለተኛ ደረጃ የትምህርት እድሎች፣ ስኮላርሺፖች እና የፋይናንስ እርዳታ በተጨማሪ ለመማር በርካታ እድሎች ይኖሯቸዋል። መጪው የኮሌጅ ፌር/የተቀናበረ-ዝግጅት እና ክውነቶች ከዚህ በታች ያሉትን ያካትታል፡-

- **እሁድ ኖቬምበር 5፣** Sunday, Nov. 5—Greater Washington, DC National College Fair—12:30–4 p.m. at the Walter E. Washington Convention Center in Washington, D.C. ከስፍራው ለመገኘት የሚችሉ ወላጆች እና ተማሪዎች ከተለያዩ ኮሌጆች እና ከበርካታ ዩንቨርስቲዎች ከሚመጡ ተወካዮች ጋር አንድ ለአንድ ተገናኝተው ኮሌጅ ስለመግባት እና ስለ ፋይናንስ እርዳታ/ድጋፍ ያሉትን እድሎች ለማነጋገርና ጠይቀው ለመረዳት እድል ይኖራቸዋል። ከዝግጅቱ ቀን አስቀድመው ይመዝገቡ በስፍራው ተገኝተው ጊዜዎትን በደንብ ለመጠቀም እና የኮሌጆቹ ተወካዮች ከእርስዎ ጋር ለመነጋገር እንዲያስችላቸው። ፌር/ዝግጅቱ ያለበት ስፍራ እንደደረሱ ለእርስዎ የሚስማማዎትን ኮሌጆች ለማግኘት ካርታ/ማፕ ይውሰዱ። በዋናነት ማጥናት ስለሚፈልጉትን የትምህርት ዓይነት ለመወሰን መሟላት ስላለባቸው ነገሮች ለመረዳት፣ ቦታዎችን እና ሌላም ማወቅ የፈለጉትን ነገር ለመርዳት ካውንስለሮች/አማካሪዎች በስፍራው ይገኛሉ። https://www.nacacfairs.org/attend/national-college-fairs/greater-washington-dc/#tab_0
- **ማክሰኞ ኖቬምበር 7፣** የኮሌጅ እና የስራ ፌር ከ 10 a.m. እስከ 1 p.m በ Bohrer Park in Gaithersburg, high school ጁኒየሮች እና ሲኒየር ተማሪዎች በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶቻቸው አማካይነት ይገባሉ።
- **ሐሙስ ኖቬምበር 9፣** ወደ ኮሌጅ መግቢያ መንገድ-ጁኒየሮች እና ወላጆች ከሜሪላንድ ዩንቨርስቲ፣ ሼዲግሮቭ ከሚገኙ ዩንቨርስቲዎች፣ እና ከሞንጎመሪ ኮሌጅ ተወካዩች ጋር ለመገናኘት ይችላሉ። በዚህ ይመዝገቡ እና Event, Montgomery College, Germantown Campus, 4–7 pm. በሚለው ላይ ጠቅ/click ያድርጉ።
- 5:30 pm በስፓኒሽ ቋንቋ ዝግጅት ይቀርባል።

MCPS Parent Academy የፋይናንስ እርዳታ/financial aid በሚመለከት አውደጥናት/ዎርክሾፕ ይካሄዳል። ከ 7–8:30 p.m **ሐሙስ ኖቬምበር 2፣** በ Quince Orchard High School, 15800 Quince Orchard Road in Gaithersburg ይካሄዳል። በኢንተርኔት ይመዝገቡ ወይም 240-314-4860 ይደዉሉ። www.mcpsparentacademy.org
**ተጨማሪ መረጃ እዚህ ይገኛል።**
http://www.montgomeryschoolsmd.org/uploadedFiles/departments/parentacademy/homepage/2017%20Fall%20PA%20Flyer.pdf
http://mde.maryland.gov/programs/LAND/RecyclingandOperationsprogram/Pages/EducationandOutreach.aspx